## 9. የሲቪል ሶሳይቲ መኅበርና የዲሞክራሲ የእድገት ግንኙነት፣

### 9. 1. የብራዚል ምሳሌ፣

በወይዘር ሃገር ያን ደሸፖኔ

የብራዚል ስፋት የፈረንሳይን 16 ጊዜ እጥፍ ሲሆን የህዝቧ ብዛት ደግሞ 145 ሚሊዮን ነው:: ባለፉት 30 ዓመታት በተለይ ከውጭ የሚገዙ ሸቀጦችን በአገር ውስጥ በሚሰሩ እቃዎች ለመተካት በተደረገው የኢንዱስትሪ እድገት ጥረት ምክንያት ሀገሪቱ ትልቅ እርምጃ አድርጋለች:: በጣምም ተለውጣለች:: ይህ ፖሊቲካ በ1964 ዓ.ም. የወታደራዊው መፈንቀለ መንግሥት ከመደረጉ በፊት የተጀመረ ፖሊቲካ ነበር:: ወታደራዊው መንግሥትም ይህ በህዝቡ ማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚያስከተለውን መዘዝ ቸላ በማለት ጥቂቶች እየከበሩ ብዙው ህዝብ ደግሞ እየደኸየ እንዲሄድ የሚያደርገውን ፖሊቲካ ገፋበት::

ለምሳሌ በ1983 ዓ.ም. ከሀገሪቱ ሃብት 46 % ያህሉ ከህዝቧ 10% ብቻ በሚሆኑት ሰዎች እጅ ነበር:: ከብራዚል ህዝብ ግማሹ ደግሞ ከሀገሪቱ ሀብት 13 ከመቶውን ለመካፈል የተገደደበት ሁኔታ ነበር:: ሃገሪቱ ዛሬም በጣም በዝባ ሁኔታ ላይ ትገኛለች:: በአንድ በኩል ከምእራቡ ዓለም 8ኛ ኃያል መንግሥት ነች ትባላለች:: በሌላ በኩል ደግሞ 121 ቢሊዮን ብር ብድር ያለባት አገር ነች:: ለዚህ ነው የሀገሩ ህዝብ ብራዚልን ከሀብታሟ ቤልጀም ከድሀው ህንድ አገር ትመስላለች በማለት "ቤልጀኢንድያ" ብሎ የሚጠራት::

ብራዚል የ27 ግዛቶች ፌዴሬሽን ናች:: እያንዳንዱ ግዛት የራሱ መንግሥት፣ የራሱ ምክር ቤት ወዘተ አለው:: እንደ ሳዖፓሎ የመሳሰሉት ከተሞች እጅግ ብዙ ህዝብ የተጠራቀመባቸው የተጣበበባቸው አካባቢዎች ሲሆኑ ሰፋፊ የሆኑ ያልተጣበቡ የገጠር አካባቢዎችም በብዛት ይገኛሉ:: በከተማም ሆነ በገጠር አካባቢዎች አመጽ የተስፋፋ ነው:: ምንም እንኳን ዘረኝነት በግልጽ ባይታይም ጥቁሮች ከህብረተሰቡ ዝቅተኛውን ቦታ ይዘው ይገኛሉ::

ወታደራዊው መንግሥት ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ ለ20 ዓመታት ያህል ቆይቷል:: ይህ አገዛዝ ከ1977 ዓ.ም. ጀምር ከፊት እያለ ከመጣ በኋላ በ1985 ዓ.ም. ወታደሮች ሥልጣን ለሲቪል መንግሥት አስረክበው ከፖለቲካው መድረክ ገለል አሉ:: በነዚህ 20 ዓመታት ውስጥ ቤተክህነት የህዝቡን ማህበራዊ ኑሮ በተለያዩ ዘርፎች በማደራጀት ትልቅ ሚና ተጫውታለች:: አብዛኛው ህዝብ ካቶሊክ በሆነባት በዚች አገር ቤተክህነት በያለበት የምዕመናን ኮሚኒቲ በማደራጀት ህዝቡ እንዲሰባሰብ፣ እንዲወያይ፣ ሃሳቡን እንዲገልጽ የሚያስችሉት መድረኮች ለመፍጠር ችላለች:: እነዚህ ኮሚኒቲያችም በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ ብቻ ያተኮሩ አልነበሩም:: የዲሞክራሲ አሠራር ልምድ ማዳበሪያ፣ የህዝብ ማስተማሪያና ማንቂያ መድረኮችም ነበሩ::

ወታደራዊው አገዛዝ ማብቂያ ላይ ከፍተኛ ድህነት በሰፈነባቸው ከተሞች ብዙ ማህበራት መቋቋምና በፌዴሬሽን መልክ እየተሰባሰቡ ለህዝቡ አስፈላጊ የሆኑት መሠረታዊ ተቋሞች እንዲገነቡ መታገል ጀመሩ:: በዚሁ አኳያ ደግሞ ጠበቆችና ጋዜጠኞች እየተደራጁ ለሰው ልጅ መብት መታገል ጀመሩ:: ቤተክህነትም በዚህ የመደራጀት ጥረት ትልቅ ሚና መጫወታን ቀጠለች::

በገጠር ዋናው ጥያቄ የመሬት ይዞታ መሻሻል ጥያቄ ነበር:: ግን ወታደራዊው አገዛዝ ከወደቀ በኋላ የተመረጡት ፕሬዝዳንት ታንክሬደ ነቬስ በዚህ በኩል እርምጃ እንዲወሰድ የአዋጅ ረቂቅ ቢያቀርቡም ባባለመሬቶች ተጽእኖ የተነሳ ይህ ረቂቅ ከሥራ ላይ ሊውል አልቻለም::

ሲቪል መንግሥት ከተቋቋመ በኋላ በ1986 ዓ.ም. የክፍለሀገር ገዥዎች፣ ሴነተሮችና የፓርላሜንት አባላት ምርጫ ተካሄደ አዲስ የሚቋቋመውም ሸንጎ የህገ መንግሥት አውጭነት መብት ነበረው:: በዚህ ጊዜ ብዙ ማህበራትና የእርዳታ ድርጅቶች፣ በቤተክህነት ጉባኤ እየተረዱ ህዝቡን ማንቀሳቀስና ማስተማር ጀመሩ:: ህገ መንግሥት ምን እንደሆነ፣ በምርጫ የሚመሰረቱት የተለያዩ ተቋሞች ሚና ምን እንደሆነ፣ የጊዜው ዋና ዋና ጥያቄዎችን በማመለከት. ...ለህዝቡ ንቃት መስጠት ጀመሩ::

ከአንዳንድ ተራማጅ የሸንጎ አባላት ጋር በመተባበር የህዝብ ጥያቄዎች እየተቀነባበሩ በጽሁፍ ይቀርቡ ጀመር:: አንድ በጽሑፍ የሚቀርብ ጥያቄ ከ30,000 በላይ ፊርማ ካገኘ የግድ የፓርላሜንት ውይይት አጀንዳ ውስጥ ይመዘገብ ነበር:: በዚህ በመጠቀም በመርቀቅ ላይ ባለው ህገ መንግሥት ውስጥ ህዝቡ መገባት አለባቸው የሚላቸውን አንቀጾች ማቅረብ ቻለ:: ከነዚህ በህዝብ ከቀረቡት ሃሳቦችና አንቀጾች አንዳንዶቹ ተቀባይነት አገኙ:: ነገር ግን የፓርላሜንቱ ብዙሀን ክፍል ኮንሰርቫቲቭ ስለነበር፣ መሬት ድልድልን የሚጠይቁ ሃሳቦች ተቀባይነት አላገኙም:: የሆነ ሆኖ ይህ ህዝብ የማስተማርና የማንቃት ተግባር ህገ መንግሥቱ ከረቀቀም በኋላ በየግዛቶቹ በተካሄዱት ስብሰባዎችና ውይይቶች አማካኝነት ቀጠለ:: ሆኖም በዚህ በሁለተኛው ዙር ውይይት የህዝቡ ተሳትፎ እንደ መጀመሪያው ዙር አልነበረም::

በብራዚል "ሲቪል ሶሳይቲው" ቀስ በቀስ በቅራኔዎችና በተለያዩ የጥቅም ግጭቶች መሀል እየተገነባ ነው:: በዜግነት መብትና በዲሞክራሲ የመጠቀም ልምዱን እንዲያዳብር በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ህዝቡን ማስተማርና መቀስቀስ በጣም አስፈላጊ ነው:: ለሥልጣን መፍካከርና የርእዮተ ዓለም ልዩነቶች፣ የተራማጅ ኃይሎችን ክፍፍልና መዳከም እንዳያስከትሉ በየጊዜው ህዝቡን የሚያንቀሳቅሱ ሀሳቦችን እያነሱ መራመድ አስፈላጊ ነው::

## 2. የኮሎምቢያ ምሳሌ፣
በአቶ ሉዊ አልቤርቶ ሬስትሬፖ

በኮሎምቢያ "ከሲቪል ሶሳይቲው" በመንግሥትና በፓርቲዎች መሃከል ስላለው ግንኙነት ማብራራት እፈልጋለሁ:: ሲቪል ሶሳይቲ በተለያዩ ማህበራት አማካኝነት የተወሰኑ ጥቅሞችን ለማራመድ በህብረተሰቡ ውስጥ የሚዘረጋ የድርጅቶች መረብ ነው:: እነዚህን የተወሰኑ ጥቅሞች የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሊታገሉላቸው ይችላሉ:: በዚህ አገላለጽ ከተስማማን በኮሎምቢያ በግልጽ የምናየው ነገር አለ:: ሀብታሙ ክፍል በአሠሪዎች ማህበር፣ በባለመሬቶች ማህበር ወዘተ በደንብ የተደራጀ ሲሆን እነዚህ ማህበራት የሚያራምዱትን ዓላማ የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሊታገሉባቸው ይችላሉ:: ወዛደሮችና ገበሬዎች ግን በቅጡ የተደራጁ ስላልሆኑ በፖለቲካው መድረክ የመወከላቸው ጉዳይ እጅግ አስቸጋሪ ነው::

እንደዚህም በመሆኑ የኮሎምቢያ "ሲቪል ሶሳይቲ" የገዥ መደቦች "ሲቪል ሶሳይቲ" ብቻ በመሆኑ ከህብረተሰቡ 15% አይወከልም:: ህዝባዊው "ሲቪል ሶሳይቲ" ደካማ ነው ያለውም ቢሆን ለፓርቲዎች መሣሪያ እንዲሆንና የነሱን የምርጫ ዓላማ ለማራመድ የተቋቋመ ነው::

የእንዲህ ዓይነቱን ሲቪል ሶሰይቲ እድገት በሶስት ደረጃ ማየት ይቻላል:: በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ ትላልቅ የገበሬና የወዛደር ማህበራት በሃገሪቱ በያለበት በተለይም በበጉታ ተቋቋሙ:: ከዚያ ከ1930 ዓ.ም. በኋላ የመጀመሪያው ትልቅ ማእከላዊ የወዛደር የሙያ ማህበር ተቋቋመ:: የዚህ ማህበር አመራር የተያዘው "ማህል ገራ" በሆኑ ኃይሎች ነበር:: በ1936 ዓ.ም. የተቋቋመው የሊብራል ፓርቲው መንግሥት ይህንን ማህበር በመደገፍ ብዙ አወንታዊ እርምጃዎች ወሰደ:: ይህንንም ያደረገው ማህበሩን ከፖለቲካ አንጻር ከቁጥጥሩ ሥር ለማዋል ነበር:: ይህም ዓላማው ተሳካለት::

ከ1950 ዓ.ም. ጀምሮ ሃገራችን የእርስ በእርስ ጦርነት ወቅት ውስጥ ገባች:: የዚህ ጦርነት ምንም ሥልጣን ላይ የወጣው ወግ አጥባቂ ፓርቲ በሊብራል ፓርቲው ላይ ባነሳሳው ጭቆና ምክንያት ነበር:: በዚህም ሳቢያ የወዛደሩ ማህበር ተፈረከረከ ብዙ መሪዎች ተገደሉ:: ይህንን ማህበር በዚህ መልክ ያዳከመው መንግሥት የሱን ፖለቲካ የሚያራምድና በቤተክህነት የሚደገፍ ሌላ የወዛደር የሙያ ማህበር አቋቋመ::

በ1960 ዓ.ም. አካባቢ ደግሞ ማርክሳዊ ሌኒናዊ የሆኑ ኃይሎች ሌላ ሶስተኛ የሙያ ማህበር አቋቋሙ:: በዚህ መልክ ገዢ መደቦቸጥቀማቸውን የሚያስከብሩባቸው የተዋሀዱ ማህበራት አቋቁመው ሲሠሩ የወዛደሩ የሙያ ማህበራት በፖለቲካ ፓርቲዎች ጨዋታ ምክንያት ተከፋፍለው ይገኙ ነበር:: ይህ መከፋፈል በወዛደሩ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በገጠሩም የሚታይ ስለነበር "ህዝባዊው ሲቪል ሶሳይቲ"ከአጠቃላይ ደካማ እየሆነ ቀጠለ ማለት ይቻላል::

ከ1975 ዓ.ም. እስከ 1985 ዓ.ም. ድረስ ባለው ወቅት በኮሎምቢያ የተከሰተው የርእዩ ዓለም ቀውስ በጠቀላላው ህዝቡ በፓርቲዎች ላይ ያለውን እምነት እንዲያጣ አደረገው:: በዚህ ወቅት ከፖለቲካ ፓርቲዎች ነጻ የሆኑ ህዝባዊ ድርጅቶች በያለበት መፍላት ጀመሩ:: ይህ ጥቅሙን በሚገባ የተረዳ፣ በዜግነቱ መብት በሚገባ ለመጠቀም የሚሻ፣ በዚህ አንጻር የአባላትን ንቃት ለማዳበር የሚጥር "ህዝባዊ ሲቪል ሶሳይቲ" መገንባት ጀመረ::

ግን ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ ሃገሪቱ በተለይ በድራግ ነጋዴዎች ቁንጮነት ሌላ የፖለቲካና የሰሻለ አመጽ ወቅት ውስጥ ገባች:: አብዛኞቹ የሲቪል ሶሳይቲው መሠረት የነበሩት ማህበራት ፈራረሱ:: እዚህ ላይ አንድ መነሳት ያለበት ነጥብ አለ:: በየአለበት የአመጽ ማየልና፣ የሲቪል ሶሳይቲው ማህበራት መጥፋት እየተያያዙ ያደጉ ክስተቶች ናቸው:: በመሆኑም ህዝባዊው ሲቪል ሶሳይቲው መልሶ እንዲያንሠራራ ከተፈለገ ሰላም ቅድመ ሁኔታ ሆኖ ይቀርባል:: ይህ ሲሆን ብቻ ነው በፖለቲካ ፓርቲዎች ቁጥጥር ስር ሳይሆን ግን በእነሱ አማካኝነት በፖለቲካው መድረክ እየተወከለ ሊያድግ የሚችል ሲቪል ሶሳይቲ ሊፈጠር የሚችለው::

## 3. የሀይቲ ምሳሌ፣

በአቶ ዣን ሁግ ሄንሪስ

ሃይቲ በ1986 ዓ.ም. ከጭቆና አገዛዝ ስትላቀቅ በሀገሪቱ ትልቅ የዲሞክራሲያዊ ተቋሞች ድክመት ነበር:: የዱቫሊዬ ሥልጣን እንደተቋቋመ ሌላ የሥልጣን ማእከል ሊሆኑ ይችላሉ የሚባሉትን ኃይሎች ሁሉ ገና በጥንስስ እያሉ መቀጨት የአገዛዙ ዋና ተግባር ነበር:: ለምሳሌ በ1961 ዓ.ም. የተማሪዎች አድማ ስለነበር ዩኒቨርስቲው ተዘጋ:: የተማሪው ማህበር መሪዎች በሙሉ ተሰደዱ:: በ1969 ዓ.ም. ደግሞ የወዛደር የሙያ ማህበራት በሙሉ ተዘጉ፣ ጋዜጦች በሙሉ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ሆኑ::

በ1971 ዓ.ም. አባትየው ዱቫሊዬ ሞተው ልጃቸው ሲተኩ ነገሮች ትንሽ ከፈት ማለት ጀመሩ:: በተለይ ደግሞ በ1977 ጂሚ ካርተር የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሲሆኑ ይኸ "ሊብራላይዜሽን" እየተጠናከረ መጣ:: አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲያች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ:: ሙሉ በሙሉ በመንግሥት የማይታወቁ የማይደገፉ የሙያ ማህበራትና የገበሬ ድርጅቶች ተቋቋሙ:: የተለያዩ የእርዳታ ድርጅቶችም በገጠር አካባቢያች መተከል ጀመሩ:: በ1980 ዓ.ም. ካርተር ባለመመረጣቸው ይህ ሂደት እንደ አጀማመሩ መቀጠል አልቻለም:: ጋዜጠኞች መታሰርና ከሀገር መባረር ጀመሩ:: የሙያ ማህበራት ህቡዐ ይሆኑ ጀመር:: ከ1976 ዓ.ም. ወዲህ የተጀመረው ሲቪል ሶሳይቲውን የመገንባት ሂደት በዚህ መልክ ተቋረጠ::

በ1983 ዓ.ም. የሮማው ጳጳስ ዳግማዊ ዮሃንስ ጳውሎስ ሃገሪቱን ሲጎበኙ "ነገሮች መለወጥ አለባቸው" ብለው የተናገሩት ለሌላ ሂደት መቀስቀስ ምክንያት ሆነ:: በጠቅላላ ተቃዋሚ ኃይሎች በዚህ መፈክር አማካኝነት ተንቀሳቅሰው ትግላቸውን ስላፋፋሙ ዣን ክሎድ ዱቫሊዬ በ3 ዓመት ውስጥ ተገለበጡ::

በዚህ ወቅት ማንኛውንም ህብረተሰቡን ለማስተማር፣ ለማንቃትና፣ ለማንቀሳቀስ የሚደረገውን ጥረት በመደገፍ ቤተክህነት ትልቅ ሚና ተጫውታለች:: በተጨማሪ ሬዲዮ ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል ማለት ይቻላል:: በተለይ የሀገሩ ህዝብ በይበልጥ በሚገባው የክሪዎል ቋንቋ ፕሮግራም በመጀመሩ ህዝቡን ለማንቃት በሚደረገው ጥረት ወሳኝ ሚና ተጫውቷል::

በዚህ ሁኔታ ቀደም ሲል የተደመሰሱት ህዝባዊ ድርጅቶች ቀስ በቀስ ማንሰራራትና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰው ልጅ መብት ጥያቄ እየተጋነነ መምጣት ለዲሞክራሲያዊ ሂደት የማይናቅ አስተዋጽኦ አድርገዋል::

ፈላጭ ቆራጩ ዣን ክሎድ ዱቫሊዬ እንደወረደ የወጣቶች፣ የቀሉያች የሴቶች ... ማህበራት መፍላት ጀመሩ:: ብዙ የገበሬ ማህበራት ተቋቋሙ:: የወዛደር የሙያ ማህበራትና የባለሙያዎች /ማለትም የሃኪሞች፣ የመሃንዲሶች፣ የእርሻ አዋቂዎች../ ማህበራት በአዲስ መልክ ተመሠረቱ::

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በፖለቲካውም መድረክ አዳዲስ ፓርቲያች፣ ከዚሁ ከሲቪል ሶሳይቲው የእድገት ሂደት ጋር አብረው መደራጀትና ሥር መስደድ ጀመሩ:: የ1987 ዓ.ም. ህገ መንግሥት በህዝብ ድምጽ የጸደቀው እንግዲህ በዚህ ሁኔታ ነበር::

ዛሬ በሃይቲ ሲቪል ሶሳይቲው ከፍተኛ ክብደት አለው:: በጤና በትምህርት ዘርፍ የሄዱን እንደሆነ እነዚህ አገልግሎቶች ከግማሽ በላይ የሚካሄዱት በማህበራትና በእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች አማካኝነት ነው::

ይህም ሆኖ ገና ሙሉ በሙሉ አሸንፍአል ማለት አንችልም:: አባ አሪስቲድ ዲሴምበር 16, 1990 ዓ.ም. ለፕሬዚዳንትነት ተመርጠዋል:: በዚህ ምርጫ አማካኝነት የተከፈተው አዲስ ምእራፍ እንዲጠናከርና ህብረተሰቡ ወደፊት መራመዱን እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል:: ሲቪል ሶሳይቲው ሙሉ በሙሉ ሚናውን መጫወት አለበት:: ይህም ማለት ሁኔታውን ለመቀልበስ ሙከራ ቢቃጣ ይህንን አስከፊ ሂደት በተደራጀ መልክ ለመቋቋም በተጠንቀቀ መጠበቅ ይኖርበታል:: በተጨማሪም በሀገሪቱ የልማት ሂደት ውስጥ እየተደራደረ የመሳተፍ ብቃችሎታ እንዳለውም ማሳየት ይኖርበታል:: መንግሥት በበኩሉ የህዝቡን መሠረታዊ መብቶች በማክበርና በማስከበር ለዚህ ሂደት መቀጠል አመቺ ሁኔታን መፍጠር ይኖርበታል::

## 4. የፖላንድ ምሳሌ፣

### በአቶ አንድሬ ክራስናውስኪ

ከፖላንድ ምሳሌ በመነሳት በአንድ ብቸኛ ገዥ ፓርቲ፤በብቸኛ የተቃውሞ ንቅናቄና "በሲቪል ሶሳይቲ"ም ሃከል ስላሉት ግንኙነቶች አንዳንድ ሃሳቦችን ለመሰንዘር እፈልጋለሁ::

አንድ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን በደንብ ለመዋጋት ከተፈለገ ከፖለቲካና ከርእዮተ ዓለም ልዩነቶች ባሻገር ተቃዋሚ ኃይሎች በአንድነት ተሰባስበው መታገል አለባቸው:: ይህ አማራጭ የሌለው ቅድመ ሁኔታ ይመስለናል:: ግን ደግሞ ጸረ ዲሞክራቲክ የሆነውን ሥርዓት ለመዋጋት የተለያዩ ኃይሎችን በዚህ መልክ የሚያሰባስበው የተቃውሞ እንቅስቃሴም በአወቃቀሩም ሆነ በአሠራሩ ዲሞክራቲክ የማይሆንበት ሁኔታ አለ::

የተቃዋሚ ኃይሎች ውህደት ብዙውን ጊዜ የሚገኘው በጋራ ዝርዝር ዓላማዎች ዙሪያ ሳይሆን ያለውን አገዛዝ በመቃወም ማለትም በአሉታዊ መድረክ ላይ ነው።ጠበቅ ያሉ ውይይቶችና ክርክሮች አይካሄዱም:: በዚህ ሁኔታ ተቃዋሚ ኃይሎች ሥልጣን ሲይዙ ሳያስቡት ከተለያዩ መንገዶች ለመምረጥ ይገደዳሉ::

ከእንደዚህ ዓይነት የትግል ሂደት ሶስት የተለያዩ ውጤቶች ሊከተሉ ይችላሉ:: የመጀመሪያው ተቃዋሚው ኃይል ሥልጣን ይጨብጥና "የሃገር ግንባታ" በሚል ሰበብ የወደቀው መንግሥት አስቀምጧቸው የሄደውን ጸረ ዲሞክራቲክ ተቋሞችና ዘዴዎች "በጊዜያዊነት" ይጠቀምባቸዋል:: በዚህ ሁኔታ እንግዲህ አዲስ "ዲሞክራሲያዊና ብቸኛ ፓርቲ" ይፈጠራል:: የሚወስዳቸውን እርምጃዎች ሁሉ የቀድሞውን ሥርዓትና ገዥዎች ለመዋጋት መጥውን ገነት ለማዘጋጀት፣ የውጭ ጠላቶችንም ለመከላከል አስፈላጊ እንደሆኑ እርምጃዎች አድርጎ ያቀርባቸዋል:: የዲሞክራሲያዊው ለውጥ ሂደት በር ይዘጋበታል:: ሌላ ፈላጭ ቆራጭ የሆነ ሥርዓት ቀስ በቀስ ይገነባል:: በተለያዩ የአፍሪካ አገሮች በኩባ የታየው ይህ ነው::

በሁለተኛው አማራጭ ሂደት ለሥልጣን የበቁት ተቃዋሚ ኃይሎች አሁንም አንድነታቸውን ይጠብቃሉ:: ግን ደግሞ በውስጣቸው ፉክክርና ሽኩቻ ይፈጠራል:: ከዚህ ሽኩቻ በአሸናፊነት የሚወጣው ኃይል ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ጸረ ዲሞክራቲክ ዓይነት ጉዳና መከተል ይጀምራል::

በሶስተኛው አማራጭ ሂደት ተቃዋሚ ኃይሎች ይከፋፈሉና "ሲቪል ሶሳይቲው" በተለያዩ ፓርቲዎች አማካኝነት ይደራጃል:: ይህ ዓይነቱም ሂደት ቢሆን በለውጥና በሽግግር ዘመን አስቸጋሪ ሁኔታዎችን ይፈጥራል ምክንያቱም የቀድሞውን አገዛዝ በመጣል በጋራ ይታገሉ የነበሩትን ኃይሎች ሊያዳክማቸው ይችላል::

እንግዲህ ከዚህ ተነስተን የፖላንድን ሁኔታ እንመልከት:: ከ1976 ዓ.ም. በኋላ ቀደም ሲል በምሁራን ተቋቁሞ የነበረው "የወዛደሮች መከላከያ ኮሚቴ" ብዙ የተለያዩ ኃይሎችን መሰብሰብ ጀመረ:: ከነዚህ ውስጥ በፖለቲካ አቋማቸው ከመሃልም ከቀኝም የነበሩ ሰዎች ቢኖሩም አብዛኛዎቹ ከኮሚኒስት ፓርቲ እየፈለሱ የመጡ፣ ሶሻሊዝም በምስራቅ አውሮጳ ከሥራ ላይ የዋለበትን ሁኔታ የሚቃወሙ የግራ ኃይሎች ነበሩ::

በ1980 ዓ.ም. ከተደረጉት የሥራ ማቆም አድማዎች በኋላ አገዛዙ የነጻ ሙያ ማህበራትን መቋቋም ስለተቀበለ፣ "ሶሊዳርቲ" ተመሠረተ:: በጠቅላላው ተቃዋሚ ኃይሎች ሁሉ

የሚፈልጉት ኃይሎች በየመስካቸው የተለያዩ ፓርቲዎች እንዲያቋቁሙ ተከራከሩ:: በመጨረሻም አሸናፊ ሆነው የሚወጡት የዋሌሳ ደጋፊዎች ይሆናሉ:: በዚህም የተነሳ ሶሊዳርቲ ተከፈለ:: የተለያዩ ፓርቲዎች ተቋቁመው የቀድሞው ሶሊዳርቲ መሪዎች በፖለቲካው መድረክ መፋጠጥ ጀመሩ::

ዛሬ በፖላንድ 92 የፖለቲካ ፓርቲዎች ተቋቁመዋል:: ግን በነዚህ ፓርቲዎች ውስጥ ከህዝቡ 4% ብቻ ነው የሚሳተፈው ለአርባ አምስት ዓመታት በአንድ ፓርቲ አገዛዝ ሥር የቆየው የፖላንድ ህዝብ በአጠቃላይ "ፓርቲ" ሲባል በጥርጣሬ ዓይን ይመለከታል::

እርግጥ ነው የሌባ ሶሊዳሪቲን እንዲህ መከፋፈላቸውና ጸረኮሙኒስት የሆነውን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ማዳከማቸው ትክክል ነበር ወይ የሚለው ጥያቄ ሊቀርብ ይችላል::መልሱ የሚገኘው ዛሬ ሶሊዳርቲ እንደ ሙያ ማህበር የሚጫወተውን ሚና በመገምገም ነው:: የሶሊዳርቲ መሪዎች በዚህ የሽግግር ወቅት መንግሥቱን እንደሚደግፉ ደጋግመው ገልጸዋል:: ግን ይህ ብዙ አባላት ያስቆጣ ፖሊሲ ሆና ይታያል:: በተጨባጭ እንደሚታየው የተለያዩ የሶሊደሪቲ ቅርንጫፎች በተለይም ደግሞ በየፋብሪካው ያሉት ህዋሶች ቀደም ሲል በኮሚኒስቶች ተረጋግጦ የነበረው ማህበራዊ መረጋጋት መቀጠል አለበት በሚል ሰበብ ለውጥ እንዳይካሄድ እንቅፋት ሲሆኑ እየታዩ ናቸው::

ይህም ሆና ዛሬ ሃገሪቱ አስቸጋሪ ሁኔታ ላይ ትገናለች የሥራ አጡ ቁጥር አንድ ሚሊዮን ተኩል ደርሷል:: በዚህም የተነሳ የሙያ ማህበሩ የወዛደሮች መብት እንዲከበርና የሥራ አጦች የኑሮ ዋስትና እንዲረጋገጥ የመታገል ግዴታ እየወደቀበት ነው::

በሚቀጥሉት ወራት የፖርላሜንት ምርጫ ይካሄዳል:: ይህ ምርጫ የሚካሄደው ሃገሪቱ በኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ እያለችና ዋሌሳ የገቡትን ቃል ባለመፈጸማቸው በህብረተሰቡ ውስጥ ማጉረምረም በበዛበት ወቅት ነው:: የዚህ ምርጫ ዝግጅት በፕሬዜዳንቱ ደጋፊዎችና በ.ፓርላሜንቱ መሃከል ግጭት እየፈጠረ ይገናል:: በዚህ በመጠቀም ኮሚኒስቶች አቋማቸውን እያጠናከሩና ሶሊዳሪቲም ከእንግዲህ እንደማይመለስ ሆና እየተከፋፈለ ነው:: ዝርዝር ውስጥ መግባት አልፈለግም:: ግን ዛሬ ባለው ሁኔታ ላይ በመመርኮዝ የሚከተለውን ማለት ይቻላል:: ፓርላሜንት ውስጥ ያሉት ኮሚኒስቶችም ሆኑ ሌሎች ዋና ፍላጎታቸው ቦታቸውን ላለመልቀቅ ስለሆነ የለውጡን ሂደት ለማቀዝቀዝ እየሞከሩ ናቸው::

እርግጥ ነው ለውጡ መጀመሪያ ላይ ህዝቡ ሶሻሊዝምን እንዳለ የመቃወምና ካፒታሊዝምን የማምለክ አዝማሚያ ያሳይ ነበር:: ዛሬ ግን በተለይ ሥራ አጥነት እንደዚህ በተስፋፋበት ሁኔታ ነገሮች እንደድሮው ጥርት ብለው አይታዩም:: እና በበኩላችን በሁለቱ መሃከል ሌላ ሶስተኛ ጉዳና ለማግኘት ጥረት እያደረግን ነው:: ዛሬ ፖላንድ ውስጥ ሠገነባት የያዘው "የሌቦች ካፒታሊዝም" ነው:: በሶሺየት ህብረትም እንደሚታየው የኢኮኖሚ ሥልጣንና ኃይል አሁንም የተያዘው በቀድሞው ኮሚኒስቶች መሪዎች እጅ ነው:: ከዚህ ሁኔታ ለመውጣት መንግሥትም ሆነ ፓርላሜንቱ በአስቸኳይ እርምጃዎች መውሰድ ይኖርባቸዋል::